**05/18/2024** **Ref # FANA_2024_00134**

# ከዐማራ ማህበራት ኅብረት በሰሜን አሜሪካ (ፋና) የተሰጠ ወቅታዊ መግለጫ

የአማራ ማህበራት ህብረት በሰሜን አሜሪካ/FANA የአማራው የህልውና ትግል ከገንዘብ ማሰባሰብ ባሻገር ጊዜውን በዋጀ መልኩ የተቀናጀ ፥ በሳልና በዕቅድ የሚመራ የዲፕሎማሲ፣ የአድቮኬሲ እና የፕሮታጋንዳ ስራ ያስፈልገዋል ብሎ በፅኑ ያምናል።

እንደሚታወሰው በማርች 3/2024 ዓ/ም ባወጣነው የአቋም መግለጫ የአማራው ወገናችን የህልውና ትግል አሁን ባለበት ደረጃ ከግለሰቦች እና የግለሰቦች ስብስብ ፈላጭ ቆራጭነት እና ተጻዕኖ ወጥቶ ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ባላቸው እና ለአመታት በአማራው ትግለ ላይ ንቁ ተሳትፎ እና አመርቂ ደጋፍ ባደረጉ ህጋዊ ድርጀቶች እንዲተካ ከመግለጻችን ባሻገር ባለፉት ሁለት ወራት ከየክፍላተሃገራቱ ባሉ የፋኖ አመራሮች “ገንዘብ እንድናሰባስብ ተወክለናል” በሚል የጎጃም፣የጎንደር፣ የወሎ፣ እና የሸዋ ድጋፍ አሰባሳቢ ነን በማለት በግለሰቦች የተቋቋሙ ኮሚቴዎች የአንድ ጊዜ ብቻ የገቢ ማሰባሰቢያ ሂደት በውጪ ያለውን አማራ ግራ ከማጋባት አልፎ ትተነው ወደመጣነው የጎጠኝነት ችግር መልሶ ሊያስገባን እንደሚችል ያለንን ስጋት በአጽንዎ መግለጻችን ይታወቃል።

ይህንንም ስጋታችንን በየክፍላተሃገራቶች ከሚገኙ የፋኖ አመራሮች ጋር በቀጥታ በመወያየት እና በማስረዳት እንዚህ በግለሰቦች የተቋቋሙ ኮሚቴዎች ከነበረው አንገብጋቢ ችግር አኳያ የተቋቋሙ ጊዚያዊ ኮሚቴዎች እንድሆኑ እና ከአንድ ዙር የገንዘብ  ማሰባሰብ በኋላ እንደሚከስሙ ያነጋገርናቸው የፋኖ አመራሮቹ አረጋገጠውልናል።

ነገር ግን እንዚህ ድጋፍ አሰባሳቢ ኮሚቴዎች ጊዜያዊ ሥራቸውን ከውነው ሲጨርሱ በመክሰም ፋንታ አቅጣጫ በመቀየር ተሰባስበው በውጪ አገር የአማራው ትግል ተወካይ ነን የሚመስል ይዘት ያለው አወቃቀር ይዘው ለመውጣት ዝግጅት እያደርጉ መሆኑን ተረድተናል። ይህ አካሄድ በህልውና ትግሉ ሌላ አሉታዊ ተፅዕኖ ከመጨመሩ ባሻገር ቀድመው ተደራጅተው እየሰሩ ባሉ ድርጅቶች ላይ ሌላ ተደራቢ መዋቅር በመፍጠር በውጪ ባለው አማራ ዘንድ መከፋፈልን እና ግራ መጋባትን እንደሚያመጣ እና ትግሉን በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚጎዳው ሁሉም ተቆርቋሪ ወገን ሊረዳው ይገባል። ከሁሉ በላይ አሳሳቢ የሚሆነው በነዚህ የጎጥ ኮሚቴዎች ውስጠ የተዋቀሩ ግለሰቦች ሙሉ በሙሉ በሚባል ሁኔታ ከዚህ በፊት በአማራ ድርጀቶች ውስጥ አባል ሆነው ተሳትፎ ያላደረጉ መሆኑ እና በግል የፈቀዱትን ከማድረግ እና ከመናገር አልፈው ሃላፊነት እና ተጠያቂነት ባለው አወቃቀር እና መድረከ ላይ ያልታዩ መሆናቸው ነው።

ከዚህ በፊት የገንዘብ አሰባሰብ አስመልክቶ ፣ የፋኖ መሪዎች ይረዱናል ብለው ያሰቧቸውን ግለሰቦች በየሚዲያው በመቅረብና መግለጫ በማውጣት አስታውቀዋል !  ያም ሆኖ  የነዚህ ግለሰቦች የስራ ሃላፊነት " ከአንድ ግዜ" በላይ እንደማይሆን ሁሉም የፋኖ መሪዎች ተናግረዋል ። ሆኖም እነዚህ ግለሰቦች በአሁኑ ሰአት፣ ከማናቸውም የፋኖ እዝ አመራር፣ ምንም አይነት የእውቅና ማረጋገጫ ሳይኖራቸው፣ እራሳቸውን በፋኖ አመራሮች እንደተወከሉ በማስመሰል፣ በውጭ ያለውን የገንዘብ፣ የህዝብ ግንኙነት (PR)  እና የእድቮኬሲውን ክፍል ጨፍልቀው ለመያዝና  የሌለውን የአማራ ማህበራት ለማፍረስ ቀን ከለሊት እየባዘኑ ይገኛሉ !! ይህንን ጸያፍ ድርጊት እና የተቀነባበረ ዘመቻ ፣ በሰሜን አሜሪካ ያለው የአማራ ማህበራት ህብረት (ፋና) በጥብቅ ያወግዛል!! !!

በተጫማሪም ፋና በውጭው ያለው አማራ የሚወክለውን የሚመርጠው ራሱ ዲያስፖራው እንጂ ሌላ አካል ሊመርጥለት እንደማይችል በፅኑ ያምናል ለዛም ጠንክሮ ይሰራል። መፍትሔውም ሁሉም ያመነበትና የተስማማበት እንዲሁም ግልፅነት፣ ሃላፊነትና ተጠያቂነት ባለው አማራዊ አወቃቀር ወይም ድርጅት መመራት አለበት ብለን በፅኑ እናምናለን። በመሆኑም የአማራ ማህበራት ህብረት በሰሜን አሜሪካ በስሩ ያሉትን በርካታ ህጋዊ እውቅና ያላቸውን የአማራ ድርጅቶች ህልውና ለመገዳደር የሚደረግ ማንኛውንም አፍራሽ እንቅስቃሴና፤ ከዚህ በኋላ በጎተ ስም የሚደረገውን የገንዘብ አሰባሰብ ሂደት በጽኑ የምንቃወም መሆኑን እየገለፅን የሚከተለውን ጥሪ እናስተላልፋለን።

1. የአማራ አደረጃጀቶች ይህን ጎጣዊና ከፋፋይ አካሄድ በመፀየፍ ከዚህ በፊት አማራዊ በሆነ ጥምረት ካበረከታችሁት አስተዋጽዎ እና ካስመዘገባችሁት ውጤት በላይ ወቅቱን በዋጀ መልኩ ለትግሉ እያደረጋችሁ ያለውን ድጋፍ አጠናክራችሁ እንድትቀጥሉ፤

2. ከዚህ በኋላ ፋኖዎቻችን ለማንኛውንም ድጋፍ በግለሰቦችና በኮሚቴዎች እንዲከወን ከማድረግ በመቆጠብ በቀጥታ ከአማራ ፌዴሬሽኖችና ማህበራት ጋር እንድታደርጉ፤

3. በውጭው ዓለም የምትገኙ አማራዎችና ኢትዮጵያዊያን የአማራ አደረጃጀቶች የሚያቀርቡላችሁን የድጋፍ ጥሪ በመቀበል ንቁ ተሳትፎ በማድረግ የሚጠበቅባችሁን ሁሉ እንድታደርጉ ስንል የከበረ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

ድል ለአማራ ሕዝብ !!
ድል ለፋኖ !!

የአማራ ማህበራት ህብረት በሰሜን አሜሪካ | Federation of Amharas in North America (FANA)

**የፋና ዓባል ድርጅቶች**

የአማራ ማህበር በሰሜን አሜሪካ (Amhara Association of America)

የአማራ ባለሙያዎች ማህበር (Amhara Professional Union)

የአማራ ማህበር በካሊፎርኒያ (Amhara Association of California, San Diego)

የአማራ ማህበር በዳላስ (Amhara People Civic Organization, Dallas)

የአማራ ማህበር በቺካጎ (Amhara Association of Chicago)

የአማራ ማህበር በሎሳንጀለስ (Amhara Association of Los Angeles)

የሚቺጋን የአማራ ማህበር (Amhara Association of Michigan)

የአማራ ማህበር በኔቫዳ (Amhara Association of Nevada)

የአማራ ማህበር በሲያትል (Amhara Association in Seattle)

የአማራ ኅብረተሰብ ቅርስ በሚኔሶታ (Amhara Heritage Society of Minnesota)

የአማራ ማህበር በጆርጂያ (Amhara Association in Georgia)

ዋሺንግቶን እና አካባቢው የአማራ ማህበር (Washington Area Amhara Association)

የአማራ ማህበር በኮሎራዶ (Amhara Association of Colorado)

የሱ ፎልስ እና አካባቢው የአማራ ማህበር (Amhara Community in Sioux Falls, SD)

የአማራ ማህበር በኦሪገን (Amhara Association in Oregon)

የአማራ ማህበር በአሪዞና (Amhara Association in Arizona)